ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተምያ ቤት ።



# ዜና ቤተ ክርስቲያን

ዘ ኢ ት ዮ ጵ ያ

# የአፄ መስቀል

## በ ዓ ል

ተ ቀ ጸ ል ጽ ጌ

ኃይለ ሥላሴ አፄጌ



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በያመቱ መስከረም ፲ ቀን በሚከበረው የአፄ መስቀል በዓል ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ጉንጉን አበባ ሲቀበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ መጽሔት በ፲፱፻፹፯ ዓ ም ለሚከበረው የአፄ መስቀል በዓል ከኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌልና የማስታወቂያ መምሪያ የጋዜጣና የሥነ ጽሑፍ ማደራጃ ክፍል ተዘጋጀ ።

አዘጋጅ ፤ ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተምያ ቤት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

ርእስ አንቀጽ ።

# የመስቀል ክብር በኢትዮጵያ

የክርስቲያኖች ኃይል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መስቀል የተገኘበት የክብር መታሰቢያ በዓል የክርስቲያን ደሴት የሆነችው የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ከሚያከብራቸው በዓላት አንዱ ነው ፤ ይህ ተወዳጅና ተናፋቂ የሆነ ብሔራዊ በዓል በየዓመቱ መስከረም ፲፮ና ፲፯ ቀን በደረሰ ቁጥር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ሞገስ አለው።የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትም በከፍተኛ ሥርዓተ ጸሎትና ዝማሬ ያከብሩታል ።

ለበዓሉ የተለየ ክብርና ሞገስ የሰጡት ሕዝቡና የቤተ ክርስቲያን ካህናት ብቻ ሳይሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር በዓሉ የሚከበርበት ወር ክረምቱ አልፎ በጋው የሚተካበት ፤ በሰማይ ሌጋ ፀሐይ ወጥታ በዓይን ሙሉ የምትታይበት ፤ በምድር ልዩ ልዩ የሜዳ አበቦች የሚፈኩበት ፤ በክረምት ተደብቀው ይኖሩ የነበሩት ልዩ ልዩ አዕዋፍ ያማረ ድምፃቸውን የሚያሰሙበት የመጀመሪያ ወር በመሆኑ የዚህ ሁሉ ሥነ ፍጥረት ውበትና ድምቀት ተደምሮ ለበዓሉ የተለየ ክብርና ጸጋ ሆኖታል ።

ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ታሪክ መሠረት የመስቀል በዓል በመንፈሳዊ ስሜት የሚከበረው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክፍለ ዓለማት በተለያየ ጊዜና ሁኔታ የሚከበር መሆኑን ታሪክ ያስረዳል ፤ ለምሳሌ ያህል በሮማውያን ዘንድ ሔረክለዮስ የተባለው ንጉሥ ወደ ፋርስ ዘምቶ ፋርስን ድል ነሥቶ ከተመለሰ በኋላ የቅዱስ መስቀል ክብር የሚል ሥያሜ ስለተሰጠው እንደ ጎርጎርዮስ ዘመን አቆጣጠር በየዓመቱ መስከረም ፲፬ ቀን ሲከበር መቆየቱ በሮም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታወሳል ።

የመስቀል በዓል በሀገራችን በኢትዮጵያ መከበር የጀመረው ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘመናት በፊት አንሥቶ ሲሆን በተለይ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት ጎልቶ ሊከበር የቻለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዳዊት በመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሥቶ ባደረገው መንፈሳዊ ጥረት ግማደ መስቀል ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ካደረገበት ከአሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን ጤፉት የተባለው የግእዝ መጽሐፍ ያስረዳል ።

ንጉሡ ዓፄ ዳዊት ግማደ መስቀልን ወደ ኢትዮጵያ ያስገባው መስከረም ፲ ቀን ስለሆነ ከዘመን መለወጫና ከዋናው የመስቀል በዓል ጋር በአንድ ወር ውስጥ አራት ብሔራዊ በዓል ማክበሩ አስቸጋሪ ሆኖ ..መፃኛቱ በየዓመቱ መስከረም ፳፮ ቀን ሲከበር ይኖር የነበረው የተቀጸል ጽጌ ወይም

www.ethiopianorthodox.org

የአበባ በዓል ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት መስከረም ፲ ቀን ከሚከበረው መንፈሳዊ በዓል ጋር በአንድነት ተጠቃሎ «የአፄ መስቀል በዓል » ተብሎ እንዲከበር ስለተወሰነ እነሆ ከዚያ ጀምሮ እስከአሁን ፣ ድረስ ንጉሡ ከመኳንንቱና ከሠራዊቱ ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከጳጳሳቱና ከካህናቱ ጋር ሆነው የመታሰቢያውን በዓል በታላቅ ክብርና ዝማሬ ያከብሩታል ።

በተለይም የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ብሔራዊ በዓልነቱን አጉልቶ የሚያሳየው ከዋዜማው ወይም ከደመራው ዕለት ጀምሮ መስከረም ፲፯ ቀን ነው በዚህ ዕለት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣችው ንግሥት ዕሌኒ በዕጣን ጢስ አመልካችነት እውነተኛውን የክርስቶስን መስቀል ከተቀበረበት ሥፍራ አስቆፍራ ያስወጣችው መሆኗን ለማመልከት በመላው የንጉሡ ነገሥቱ ግዛት የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአጥቢያው ደመራ እየደመረ ችቦ እያበራ በአንድ አንድ ቦታም ጅራፍ እያጮኸና ልዩ ልዩ ትርኢት እያሳየ ያከብረዋል ።

ይልቁንም በአዲስ አበባ ከተማ ስለመስቀል ክብር የሚደረገውን ልዩ ልዩ ዝግጅትና የሚታየውን አስደናቂ ትርኢት ገልጾ ለመናገር አንደበት አይገኝም ቃልም ያንሳል ስለ መስቀል ክብር በአዲስ አበባ ከተማ የሚደረገውን ታላቅ ዝግጅት ለመመልከት ከ፲፬ የኢትዮጵያ ጠ/ግዛት ወደ አዲስ አበባ የሚጎርፈው ሕዝብ ቁጥር እጅግ የበዛ ነው ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከልዑላን መሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ከጳጳሳቱና ከካህናቱ ጋር ሕዝቡ ከሠራዊቱ ጋር ሆነው በመስቀል አደባባይ በመገኘት ለሥነ በዓሉ የተለየ ክብር ይሰጡታል ።

ሕዝቡና ሠራዊቱ በየመልኩ በቡድን በቡድን ተከፋፍለው ከፀዓዳ የሀገር ልብሳቸው ፣ ከተቀጣጠለው ችቦ አቻውና ከልዩ ልዩ መንፈሳዊ መዝሙራቸው ጋር በየቡድናቸው የመስቀልን ሁኔታ የሚያስረዳ ልዩ ልዩ ቅርጽና ምስል ሠርተው በመስቀል አደባባይ የተደመረው ደመራ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ተባርኮ በንጉሠ ነገሥቱ ከተቀጣጠለ በኋላ የተጠቀሱት ወገኖች በየተራ ደመራውን እያቀጣጠሉ በመዞር ወደ የአድራሻቸው አልፈው ሲሄዱ የተመለከቱ ዓይኖች ብፁዐን ናቸው በኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝቡ ዘንድ ከዚያን ጊዜ የሚበልጥ ደስታና ብሔራዊ በዓል ያለ መስሎ አይታይም ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአባቶቹ የወረሰውን ሃይማኖቱንና መንፈሳዊ ባህሉን አጉልቶ የሚያሳይበት በዓመት ውስጥ አልፎ አልፎ የሚያከብራቸው ልደትንና ጥምቀትን የ መ ሳ ሰ ሉ ታ ላ ላ ቅ በዓላት መ ኖ ራቸው ባይዘነጋም ለመላው ዓለም መድኃኒት እውነተኛው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ስለሆነ የመስቀልን በዓል ለማክበር በሚያሳየው ከፍተኛ ክርስቲያናዊ ስሜት ኢትዮጵያ «የክርስቲያን ደሴት» ለመባሏና ሕዝቡም ጥንታዊ ክርስቲያን ለመሆኑ የበለጠ ማስረጃ ነው ግን በዚህ ፣ የመስቀል በዓል በሚከበርበት ዕለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቢሆን ፀብ ክርክርን አጥፍቶ አምልኮ ባዕድን ትቶ ከመንፈሳዊ ደስታው ጋር የክርስቶስን መከራ መስቀል ሊያስብ ይገባዋል ።

# ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ለዘመን መለወጫ ያሰሙት ቃለ በረከት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፣

« ሐድሱ መንፈሰ ልብክሙ ፣ ወልበስዎ ለሐዲስ ብእሲ ዘሐደሶ እግዚአብሔር በጽድቅ ወበርትዕ ወበንጽሕ ።

የልቡናችሁን ሐሳብ አድሱ ፣ እግዚአብሔር በሃይማኖት ፣ በቅንነት በንጽሕና ያደሰውን አዲስ ሰውነት ልበሱ ። ኤፌሶን ምዕ ፬ ቁ ፳፫ እና ፳፬ ።

እግዚአብሔርን የምትወዱ እግዚአብሔር የሚወዳችሁ ምዕመናን ሆይ ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ወስኖ በጊዜ ከፍተኛ መሥመር ዓውደ ዓመት በተባለ ክበብ ውስጥ የተመደበውን የቁጥር ሕግ ጠብቆ ሰዓት አሳልፎ ሰዓት ፣ ዕለት አሳልፎ ዕለት ፣ ወርኀ አሳልፎ ወር ፣ ዓመት አሳልፎ ዓመት ፣ መተካት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ አሁን ተለምዶ የኖረ ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚኖር ነው ።

የጊዜ አሮጌ የለውም ጊዜን ይወዳደረዋል ባይባልም በቁጥር የበዙ ክፍሎች እንዳሉት እንደ አንድ ታላቅ ቤት አድርገን ብንመለከተው እሱን ለመጎብኘት በተፈጥሮ ወደ ውስጡ የገቡ ሁሉ ጉብኝታቸውን ሳይጨርሱ ያዩትን ወደኋላ ተመልሰው ያላዩትን ወደፊት ደርሰው ለማየት ሳይችሉ ማለፋቸው ትዝ ሊለን ይገባል ፣ ሰዓት አልፎ ሰዓት ፣ ዕለት አልፎ ዕለት ፣ ወር አልፎ ወር ፣ ዓመት አልፎ ዓመት የሚታከል ቢሆንም እስከ አሁን የተደገመ ሰዓት ፣ ዕለት ፣ ወር ፣ ዓመት የለም ፣ በዚህም መሠረት ዛሬ ብለን የምንጠራው ሁለት ተመሳሳይ ቀን በቁጥር ሕግ ውስጥ አልታየም እንግዲህ ሰዓቱም ፣ ዕለቱም ወሩም ዓመቱም አዲስ ከሆነ አሮጌ ነገር የለምና እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ በማለት ፈንታ እንኳን ለዓውደ ዓመት አደረሳችሁ ብሎ መናገሩ የሚመረጥ ይመስላል ፣ እንግዲህ ዓመት አሳልፈን ዓመት መተካታችን ከሆነ የጊዜን መልክ የሚያበላሹ ጊዜን አሮጌ አስመስለው የሚያሳዩ ነገሮች በሰው ጠባይ ውስጥ መኖራቸውን እናስብ እነዚህም ክፉ አሳብና ከክፉ አሳብ ምንጭነት የሚገኙ ነፍስ መግደል ፣ ዝሙት ፣ መስረቅ ፣ በሐሰት መመስከር ስድብ ናቸው ። እነዚህ ሰውን ያረክሳሉ እነዚህና የሚመስሏቸው ሁሉ የሰው ዘር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ዘር ብዛት ሳይለውጣቸው ፣ ሳያሻሽላቸው የሚኖሩ አሮጌዎች የሰውንም ባሕርይ ያሳደፉና ያስረጁ የሚያስረጁ በሽታዎች ፣ ናቸው ።

ልዑል እግዚአብሔር እርሱን አስመስሎ በሃይማኖት ፣ በቅንነት ፣ በንጽሕና አስጊጦ የፈጠረውን የሰውን ባሕርይ ያበላሹ መልኩን የለወጡ እነዚህ ናቸው ፣ ሰው በኃጢአት የተበላሸውን ሕይወቱን በንሥሐ አድሶ አዲስ ሰውነት ለብሶ ካልተገኘ የሰዓት ፣ የዕለት የወር፣ የዓመት መታደስ እርሱን ለማገልገል የተፈጠሩ ቢሆኑም እንኳን መፈራረጃ ይሆን በታል እንጂ አይጠቅመውም፣ ከአዲስ ዓመት ደርሰናል፣

www.ethiopianorthodox.org


እግዚአብሔር ይመስገን ደስ ሊለን
ይገባል ፤ ግን አስተሳሰባችን ምን
ድነው? ቅዱስ ጳውሎስ « ቁጣን ፤
ክፋትን ፤ ስድብን ተው የሚያሳፍር
ነገር የማይገባ ነገር ከአፋችሁ አይ
ውጣ ወንድሞቻችሁንም አትክዱ ፤
አሮጌውን ሰውነት ከነሥራው ተው
ት ፤ ፈጣሪውን የሚመስለውን በአ
እምሮ የጸናውን አዲሱን ሰውነት
ልበሱ»ይላል ፤ አፍአዊው ሰውነታ
ችን እርጅና ይስማማዋል ፤ ኃጢ
አት ይስማማዋል ፤ ውስጣዊው
ሰውነታችን ግን በአእምሮ ከጠበ
ቅነው ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ
ሲታደስ ሊኖር ይችላል ፤ ይህች
ውም አርአያ እግዚአብሔር ነፍስ
ናት ፤ እንግዲያ አዲስ ዓመት ከመ
መኘት አዲስ ሰውነት መመኘት
ይሻላል፤ የሰው ዘር ዱሮም ሆነ
አሁን በማጣት ላይ ያለው ይኸንኑ
ነው ፤ አዲስ ሰዓት ፤ አዲስ ቀን ፤
አዲስ ወር ፤ አዲስ ዓመት አልታ
ጣም አዲስ ሰውነት ግን አልተገኘ
ም ፤ ምክንያቱም ሰው ባሕርዩን
ከሚያሳድፉበት ከሚያደክሙበት ፤
ከሚያስረጁበት ከክፉ አሳብና ከክፉ
ሥራዎች መለየት ስለ አቃተው ነው፤
የመላው ሰው ዘር ችግር ይህ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ አንድ ጥያቄ ልጠ
ይቅ አሁን የአዲሱ በዓል አከባበር
መከፈቱ ነው ፤ ልባችሁ ወዴት ለመ
ሔድ ምን ለማየት አስቧል ፤ ወደ
ጨለማ ወይስ ወደ ብርሃን ፤ ወደ
ኃጢአት ወይስ ወደ ጽድቅ ፤ ወደ
ክርስቶስ ወይስ ወደ ጣኦት ፤ ወደ
ኃዘን ወይስ ወደ ዘፈን ፤ ወደ ቤተ
ክርስቲያን ወይስ ወደ ሌላ ቦታ ?
እነዚህ ነገሮች ልታስቡባቸው የሚ
ገቡ ነገሮች ናቸው ።

በዓላችን የሚጠቅም መንፈሳዊ
መሆኑ ቀርቶ የማይጠቅም ሥጋዊ
የክብር መሆኑ ቀርቶ የኃሣር ፤
የጽድቅ መሆኑ ቀርቶ የኃጢአት ፤
የሃይማኖት መሆኑ ቀርቶ የክህደት፤
የንስሐ መሆኑ ቀርቶ የበደል ፤
እንዳይሆን መጠንቀቅ ያሻልና የል
ቡናችሁን አስተሳሰብ አድሱ ፤ እግ
ዚአብሔር በሃይማኖት ፤ በቅንነት፤
በንጽሕና ያጸናውን አዲሱን ሰው
ነት ልበሱ ፤ ከክፋት ወደበጎነት
ተመለሱ ፤ መርምሩ እግዚአብሔር
የሚወደውን መርጣችሁ ሥሩ ።

የሰው ጠባይ በአእምሮ ካልታደሰ
በፍቅር ፤ በሃይማኖት ካልጐለመሰ
አዲስ ዘመን ሊኖር አይችልም ፤
ለአዲስ ዓመት አዲስ ሰውነት ያስ
ፈልጋል ፤ ሁላችሁም ለአዲስ ሥራ፤
ለአዲስ ሕይወት በፍቅር ፤ በሃይማ
ኖት ተዘጋጁ እግዚአብሔር ዓውደ
ዓመቱን ይባርክልን ።

የበረከት ባለቤት እግዚአብሔር
አበውን ባርኮ እንዲባርኩ በረከትን
እንዲሰጡ ተሰይመዋል ፤ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ባር
ኮ እንዲባርኩ ስለሾማቸው ቤተ
ክርስቲያን በረከትን ለምዕመናን
ትሰጣለች ፤ ለዚህም ዕለት በረከት
አለው ከበረከት ዕለታት አንዱ
ተባርኮ በረከት የሚሰጥበት የሚገ
ኝበት ይህ የዘመን መለወጫ ዕለት
ነው፤ነቢዩ ዳዊት «ወትባርክ አክሊ
ሊለ ዓመተ ምሕረትከ የምሕረትን
ዓመት መጀመሪያ ትባርካለህ»ይላል
አክሊል ክብ ነው ይህም ዕለት የዓ
መት ክብ ዙሪያ መጀመሪያ መፈ
ጸሚያ ስለሆነ አክሊል ብሎታል ፤
ዓውደ ዓመት ማለት ነው ፤ በዚህ
ዕለት በረከት የበረከት ባለቤት እግ
ዚአብሔር ዓለሙንና በውስጡ ያለ
ውን አገራችንና ሕዝቧን ቤተ ክርስ
ቲያንና ምዕመናንን እንዲባርክ ቅዱ
ስ ስሙን ጠርተን እንለምነዋለን
ብሩክ እግዚአብሔር ዓለሙንና ከ
ውስጡ [illegible]



ቡሩክ እግዚአብሔር አገራችንንና
ሕዝቧን ይባርክ ፤ ቡሩክ እግዚአ
ብሔር ቤተ ክርስቲያንንና ምዕመ
ናንን ይባርክ ፤ ዝናሙን ነፋሱን
የምድሩን ፍሬ ይባርክ ፤ ያብዛ
ያብጅ ለጸጋብ ለበረከት ለሕይወት
ለምሥጋና ያድርገው ፤ በጋብቻ
የተሳሰሩትን ወንዶችን ሴቶችን ፤
ልጆቻቸውንም ይባርክ የተወለዱ
ትን ያሳድግ ያደጉትንም ከክፉ
ነገር ፤ ከክፉ ግብር ይጠብቅ ፤ በን
ጽሕና ፤ በድንግልና ያሉትን ይባ
ርክ ፤

ትዕግሥቱን ይሰጣቸው ፤ የካህና
ቱን ክህነት ፤ የትጉሐችን ሥራ
የገበሬውን አዝመራ ፤ የነጋዴው
ንም ወረት የሁሉንም ሥራ በቸር
ነቱ ይባርክ አገራችንን ኢትዮጵያን
ስሙ በሃይማኖት የሚጠራባቸውን
አውራጃዎቹን ሁሉ በቸርነት ይባ
ርክ ፤ መንገድ የወጡትን በባሕር ፤
በየብስ ፤ በዓየር የሚጓጓዙትን ፤
ይጠብቅ ፤ በሰላም ወደቤታቸው
ይመልሳቸው የታመሙትን ይፈው
ስ ለሙታን ዕረፍተ መንግሥተ
ሰማያትን ይስጥ ንጉሠ ነገሥታ
ችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በቸ
ርነቱ ይጠብቅ ፤ መንግሥቱን ሕዝ
ቡንና ሠራዊቱን ይባርክ ፤ ቤተ
ክርስቲያንን ያጽና በሃይማኖት ፤
ጸንተው በንጹህ ልቡና መብዓ የሚ
ያቀርቡትን ልመናቸውን ይቀበላ
ቸው ፤ ኃጢአታቸውን ያስተሥር
ይላቸው የቤተ ክርስቲያን በሮች
በሃይማኖት እንዲከፈቱ ያድርግ ፤
የተበተኑትን ወገኖችንም ይሰብስብ
የተሠሩትን ያጽና የፈረሰውን ያድስ
የወደቀውን ያንሳ ፤ ያላመነውን
ወደሃይማኖት ያቅርብ ፤ ያመኑት
ንም በሃይማኖት ያጽና ፤ ዕጣን ፤
ወይን ፤ ዘይት ሌላውንም ንዋየ
ቅድሳት ለመስጠት የሚያስቡትን
በቸርነቱ ይባርክ ክብር ምስጋና
ለቅዱስ ስሙ ይሁን ፤ ሀብት በረ
ከት የሱ ገንዘብ ነውና ።

አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ተቀጸል ጽጌ ፤

ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሲያሠራ ፪ አዕማድ አሠራ የአንዱ አምድ ቁመት ፲፰ ክንድ የዙሪያውም መጠን ፲፪ ክንድ ነበር ። በቀኝ በኩል ያቆመውን ዓምድ ያቁም ብሎ ጠራው ፤ በግራ በኩል ያቆመውንም በለዝ ብሎ ታል ለነዚህ ዓምዶች ጉልላት አሠርቶ እያንዳንዱ ሁለት መቶ የሮማን አበባ መልክ ሥሎበታል ብሎታል፤ በወለሉ ላይ በነበሩት ዓዕማድ ጉልላቶች የሱፍ አበባ የሚመስል ፬ ክንድ አድርጎ አስቀርጾ ነበር ፤ መ፡ነገሥት ቀ፡ም፡ ፯ ከቁ፡፲፫—፳፭ ከዚህም አይያይዞ በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ከወርቅ የተሠሩ አበቦች እንደነበሩ ይነገራል ፤ ቁ፴፱ ፤ ይህ አነጋገር የሚያስረዳው ጥበበኛው ንጉሥ የተፈጥሮ አበባ በተወሰነ ጊዜ አብቦ የሚረግፍ መሆኑን ስለተረዳ ዓይኑ ከአበባ እንዳይለይ አበባን የማየት ፍላጎቱ እንዳይገታበት ለሁሉ ጊዜ ማለት ዓመት፤ እስከ ዓመት የሚያገለግል የማይጠወልግ ፀሐይና ውርጭ የማያደርቀው ። የማይረግፍ ሰው ሠራሽ አበባ ከወርቅና ከብር አሠርቶ ፤ በቤተ መቅደስና በቃቤቱ ያስቀምጠው እንደ ነበር ታሪኩ ያስረዳል ።

መላው ዓለምም የሰሎሞንን ምሳሌነት በመከተል እንደየ ክፍለ አሕጉሩ ባሕልና ልማድ ዕንግዳ ሲመጣ የአበባን ጉንጉን በማስቀመጥ እቅፍ አበባ በማበርከት በየደጃፉና በየመስኮቱ አበባ በመትከል ዓመት በዓል ሲሆን በምግብ ጠረጴዛ ላይ በአበባ ዋንጫ ከያይነት ቀንጥቦ በማስቀመጥ በሰርግም ጊዜ ፤ ለሙሽራውና ለሙሽራይቱ ዕቅፍ አበባ በመስጠት ባህሉንና ልምዱን አክብሮ ይዞት ይኖራል ።

እንግዲህ የአበባ በዓል አከባበር በኢትዮጵያ የተለመደ ቢሆንም በይበልጥ ጎልቶ የታወቀው፤ በዓዜ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው ፤ ተቀጸል ጽጌ የሚለውን ግዕዛዊ ቃል የገሰሰውና የደረሰው የቅኔና የዜማ ምንጭ የነበረው ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ መሆኑን የታሪክና የባህል ተከታታይ የቤተ ክርስቲያን ፤ ሊቃውንት ያስረዳሉ የደረሰውም በ፮ኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ፤ በዓዜ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት መሆኑ ይታመናል ። በዓሉም ይከበር የነበረው መስከረም ፳፭ ቀን ነው ፤ ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥርዓት መስከረም ፳፭ ቀን ጨለማውና አስፈሪው የክረምቱ ወራት አልፎ ፤ ብርሃንን የተጎናጸፈው በአበባ የደመቀውና ያሸበረቀው የመፀው ወራት የሚተካበት ዘ፟መን በመሆኑ ነው ። ለምሳሌ ንብ ከልዩ ልዩ አበባና ዕፀዋት ቀስማ ጣዕሙ የሚጣፍጥ ማርን ለተጠቃሚው የሰው ልጅ ስታበረክት ትኖራለች ታላቅ ባለውለታችን ናት ፤ ድምፁ እንደንብ አውራ ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ ያሬድም ሥነፍጥረትን ከሚያስረዱ ከብሉያትና ከሐዲሳት ከሊቃውንት መጻሕፍትና ከልዩ ልዩ የዓይን መጻሕፍቶች የምሥጢር አበባን ቀስሞ ላህዩና ወዙ የሚያስደስት ምሥጢሩ እንደማር የሚጣፍጥ የዜማ ድርሰትን


www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚአብሔር መመስገኛ ፤ ሲያበረክት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዓፄ ገብረ መስቀል ቤተ መንግሥት ሂዶ ከዙፋኑ ፊት በሥነ ሥርዓት ቆሞ በአማረው ድምፁ ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ዓፄጌ በማለት ግሡን በለዘብ አለዝቦ አሸብሽቧል ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በቤተ ክህነትና በቤተ መንግሥት መካከል ያለው የአበባ በዓል የአከባበሩ ሥነ ሥርዓት ከ፲፫ኛው መቶ ዘመን እስከ ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ድረስ በዚህ ዓይነት ይከበር ነበር ፤

በዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ በነገሥታት ፤ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ የምትኖር አገር በመሆኗ በንጉሡ በዓፄ ዳዊት ድካምና ብርታት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል መስከረም ፲ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ስለገባ የዓፄ መስቀል ተብሎ ራሱን የቻለ በዓል ሆነ ። ኢትዮጵያ ምንጊዜም በነገሥታት ልጆቿ እንዳበበች ፍሬ ሃይማኖትን ፤ ከጀግንነት ጋር እንደያዘች ኑራለች ወደፊትም ስታብብ ስታፈራ ትኖራለች በዚህ ምክንያት በአንድ ወር ውስጥ ሁለት በዓል ተከታትሎ ከሚከበር መስከረም ፳፩ ቀን ይከበር የነበረው የተቀጸል ጽጌ በዓል ወደኋላ ተመልሶ ግማደ መስቀሉ ብገባበት በመስከረም ፲ ቀን ይከበር ብለው፣ ሊቃውንቱና መኳንንቱ የተስማሙበትን ንጉሡና ጳጳሱ ስለ ተስማሙበት የዓፄ መስቀልና መስከረም ፳፩ ቀን ይከበር የነበረው የተቀጸል ጽጌ በዓል ስሙ ሳይለወጥ ተጠቃሎ መስከረም አሥር ቀን በጋለ ስሜት ሲከበር ይኖራል ።

ከላይ እንደ ተገለጠው ሁሉ ኢትዮጵያ አገራችን በነገሥታት ልጆቿ የምትኮራ አገር በመሆኗ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትም በትምህርት ያበበችበት በዕውቀት የጎለመሰችበት በጥቡብ አበባ የተራቀቀችበት ውበቷ የታደሰበት በዓለም ነገሥታትና ሕዝብ ዘንድ የታወቀችበት ለታሪክ ጸሐፊዎችና ለጋዜጠኞች ያለፈውን ታሪክ ያስረዳችበትና የገለጠችበት አሁን የምትሠራውን በግልጥ የምታሳይበት ጊዜ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በታላቁ ንጉሠ ነገሥቱ በግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ አስተዋይነትና እርቆ ተመልካችነት ለብዙ ዘመናት በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥር ሁና መብቷን አጥታ ከኖረች በኋላ ዛሬ በያዝነው በ፳ኛው ክፍለ ዘመን ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሥር ወጥታ ራሷን ችላ ፓትሪያርክ እንድ ትሾምና ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋራ እኩል መንበር እንዲኖራት ሆኖ በሥልጣን ያበበችበት ፍሬ ሃይማኖቷን ለዓለም የገለጠችበት ዘመን መሆኑ በጉልህ ይነበባል ይህም በ፲፱፻፴፫ ዓ ም ግንቦት አንድ ቀን የተፈጸመው የፓትሪያርክነት ሹመት በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ድካምና ጥረት የተገኘ የሃይማኖት አበባና ፍሬ ስለሆነ አበባ የደስታ መግለጫ እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያንም ባለውለታ ስለሆነች መስከረም አሥር ቀን በሚከበረው የዓፄ መስቀል በዓል ከአባቶቸ ሊቃውንት



በተቀጸል ጽጌ በዓል ካህናቱ ጥንግ ድርብ ለብሰው ሲያሸበሽቡ



www.ethiopianorthodox.org

ሲያያዝ በመጣው ባህል መሠረት ደስታዋን የበዓሉ ተደራቢ አድርጋ የሰማይ ከዋክብትን የምድር አበቦችን የመሰሉ በድምፃቸው ፤ በሰልፋቸው ደስ በሚያሰኙ መዘምራን «ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ አፄጌ» እያለች የተሰማትን ደስታ በሽብሸባ ትገልጣለች ።

ባንድ በኩል ደግሞ ወሩ የዘመን መለወጫ ስለሆነ የሰው ልጅ በሥራ ግብር እምግብር የሚለወጥበት በአለፈው አመት የሠራውን የሥራ ፍሬ አጠቃሎ ሂሣቡን ዘግቶ በአዲስ ሕይወትና መንፈስ አዲስ ሥራ የሚጀምርበት በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ተሠማርቶ ከምድር ባገኘው ትምሕርት የሚጠቀምበት ዘመን ነው ለምሳሌ ምድር በመፀው ወራት ያስገኘችውን አስደሳች አበባ ወደፍሬ ለውጣ ለተተኪው ለበጋ ታስረክባለች ።

ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሃይማኖት ብቻ ደጋፊ ሳትሆን የልማት ሥራም ተባባሪና ደጋፊ ስለሆነች ፤ « የተኛችሁ ከእንቅልፋችሁ ንቁ የተቀመጣችሁ ለሥራ ታጥቃችሁ፤ ተነሡ ። ወደወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ» ባለው መሠረት የሥራ መቀስቀሻ ይሆን ዘንድ «መከሩ ብዙ ነው ሠራተኛው ጥቂት ነው ባለመከሩን ለምኑት ሠራተኛ ይጨምር ዘንድ እያለች ታሰማለች ። ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች አባቶችና ወንድሞች እናቶችና እኅቶች እንዲሁም ቤትምህርት ቤት ያላችሁ ወጣት ተማሪዎች ምክሩን ተቀብላችሁ አበባነታችሁን ወደፍሬነት እንድትለውጡት ቤተ ክርስቲያን ምክሯን ትለግሳለች ።

መምህር ሀብተ ማርያም ደስታ ።



# የዓፄ መስቀል ፤

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ግማደ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ አስቀድሞ በዓፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት በሀገሪቱ ላይ ረኃብ በሽታ አባር ቸነፈር ዛር ጋኔን በአንድ አንድ ቦታ ሰዎችን ያጠቃ ነበር ይባላል በግዕዙ ወበሀገረ ኢትዮጵያ ፀንዓ ረኀብ ወብድብድ አባር ወቸንፈር ዛር ወጋኔን ይላል ።

ንጉሡ ዓፄ ዳዊትም ይህን ነገር ለማስወገድ አቡነ ፊልጶስን ከደብረ ቤዘን አቡነ ኂሩተ አምላክንና አቡነ በትረ ማርያምን ከጣና ደሴት አስመጥተው በሽታ በሀገራችን ጸና ምን ይመስላችኋል ፤ ብለው ቢጠይቋቸው የክርስቶስን ዕፀ መስቀል ከኢየሩሳሌም ያስመጡ ያን ጊዜም በሽታዎች ሁሉ ይጠፋሉ አሏቸው ።

ይህንማ ቀደም ብየ አስቤበታለሁ አሁንም በመላላክ ላይ ነኝ ፤ በማለት መልሰውላቸዋል ። ወዲያው ለእስክንድርያና ለቁስጥንጥንያ ለኢየሩሳሌም ባለሥልጣኖች የክርስቶስን ግማደ መስቀል ከነሥርዓቱ እንዲላክልኝ እኔም በመልካም አቀማመጥ አስቀምጠዋለሁ ብለው መስከረም ፲ ቀን ደብዳቤ ልከዋል ። እነሱም በደስታ ተቀብለው ፈቅደው መልሱን ጽፈውላቸዋል ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ዓፄ ዳዊት በዓመቱ መስከረም አሥር ቀን ሊቃውንቱንና ካህናቱን ሰብስበው አስመክረው ዘጠኝ መነኮሳት አስመርጠዋል ። መነኮሳቱም ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

፩ኛ/ አባ ኂሩተ አምላክ ዘደሴተ ጣና፤
፪ኛ/ አባ እንድርያስ ዘደሴተ ፤ ጣና
፫ኛ/ አባ ዮሐንስ
፬ኛ/ አባ በትረ ማርያም
፭ኛ/ አባ ታዴዎስ
፮ኛ/ አባ ያፍቅረነ እግዚእ
፯ኛ/ አባ ዘካርያስ
፰ኛ/ አባ ያሳይ
፱ኛ/ አባ ቶማስ ሲሆኑ ፤

አሥረኛውም አቡነ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን ናቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ዓፄ ዳዊትም እኒህን መነኮሳት የፍቅርና የሰላም ደብዳቤ አስይዘው ስንቃቸውንና ጠባቂ ወታደር አድርገው መስከረም ፲ ቀን ልከዋቸዋል ። በግዕዙ ወበዛቲ ዕለት አመ አሥሩ ለመስከረም ፈነዎሙ ዓፄ ዳዊት ለተሳቱ ቅዱሳን ወለተሳቱ ከዋክብት ምስለ ፊልጶስ ዘቢዘን ይላል መስቀረም ፲ ቀን በዚችው ዕለት ዓፄ ዳዊት ዘጠኙን ቅዱሳን ከፊልጶስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ላኳቸው ማለት ነው ወሖሩ ከመ ያምጽኡ መስቀሎ ለኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ እምኢየሩሳሌም ኀበ ፤ ኢትዮጵያ የአይሁድ ንጉሥ የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀሉን ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ያመጡ ዘንድ ሁሉም በአንድነት ሄዱ ።

እኒህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘረው ቅዱሳንም ከንጉሡ በታዘዘው መሠረት ይህን ረዥም መንገድ ተጉዘው ደብዳቤ ሊቶጸፈላቸው ባለ ሥልጣኖች መልዕክቱን ካቀረቡ በኋላ ስለ ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መሄድ ተነጋግረዋል ። የኢየሩሳሌሙ ጳጳስም በደስታ



www.ethiopianorthodox.org

ተቀብሎ ግማደ መስቀሉ ከነ ሥር
ዓቱ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ ፈ
ቃዱ ሆነ በከተማው ተሰማ በዚ

ህን ጊዜ ወከልዕዎሙ ጠቢባነ ኢ
የሩሳሌም ለዕፀ መስቀሉ ወድኀ
ሬሁ ሠረቀ ብርሃን በላዕለ መስቀሉ
ይላል ወዲያው ይህን ወሬ የሰሙ
የኢየሩሳሌም ሊቃውንት መክረው
አይሆንም አይሄድም ብለው ከለ
ከሏቸው ይባላል ።

ይሁን እንጂ ከግማደ መስቀሉ ብ
ርሃኝ ቀገሰጹ ተአምራትም ተአየ
ከዚህ በኋላ ሊቃውንቱ መክረው
ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ በአንድ
ቃል ተስማምተው ተላይተዋል ።
ቅዱሳኑም ይህ ከሆነ በአሥረኛው
ቀን ግማደ መስቀሉን ከነ ሥርዓቱ
ተቀብለው በክብር ተሸኝተው ይ
ዘው መጥተዋል ።

እነሱም ግማደ መስቀሉን ከነ
ሥርዓቱ ይዘው ሲመጡ በያደሩበት
ቦታ ብዙ እርዳታ እየተደረገላቸው
ነበር ይባላል ። በደህና የመምጣ
ታቸው ወሬ በተሰማ ጊዜንጉሡ ዓፄ
ዳዊት ሠራዊታቸውን አሰልፈው
ከመናገሻ ከተማቸው ከሸዋ ወደ
ምናር ከተማቸው ተጉዘው መስ
ከረም ፲ ቀን ከመነኰሳቱ እጅ ግማ
ደ መስቀሉን ከነ ሥርዓቱ ተቀ
ብለዋቸዋል ።

ከመስቀሉም ጋር የመጡት ን
ዋያት ሐያ ሰባት ናቸው ዝርዝራ
ቸውም ከአፄ ዳዊት ታሪክና መስ
ቀል ዘዮም ከ ጊ ሉ ው
የታሪክ መጽሐፍ ይገኛል ይኸው
ም የሚገኘው ከዳጋ እስጢፋኖስ
ገዳም ነው ።

ንጉሡም በጣም ስለ ተደሰቱ
ከአባቶቻቸው ቡራኬውን ተቀብ
ለው ለካህናቱና ለሊቃውንቱ

ብዙ ሽልማትን አድርገዋል ።
ለድሆችም የሚገባቸውን ስጦታ
ሰጥተዋል ። በዚህን ጊዜ የግማደ
መስቀሉ መምጣት በመላ ኢትዮ
ጵያ ተሰማ የኢትዮጵያ ሕዝብም
ግማደ መስቀሉን ከነሥርዓቱ መ
ምጣቱን ስለ ሰሙ በይበልጥ ተ
ደሰቱ (በደስታ ተቀብለውታል) ።

በሀገሪቱ ላይ ሕዝቡን ያጠቃ
የነበረው በሽታ ጠፍቷል ከዚ
ያን ጊዜ ጀምሮ በመስቀል
ኃይል ሀገሪቱ በረከትን አግኝታ
ለች ይህ የክርስቶስ ግማደ መስ
ቀል በገባ በዓመቱ ካህናቱና ሊቃ
ውንቱ መሳፍንቱና መኳንንቱ መ
ክረው መስከረም ፲ ቀን በዓለ
ማርያም ወበዓለ መስቀል ዘዮም
በማለት ግማደ መስቀሉን አክብ
ረዋል ። በዚሁም ዕለት ግማደ
መስቀል የዓፄ መስቀል ተብሎ
ተሰይሟል ። መስከረም ፲ ቀን
እንዲከበር ሊቃውንቱና መሳፍን
ቱ የተስማሙበት ዓፄ ዳዊት የተ
ወለዱበት የነገሡበት ጠላታቸውን
ድል የነሡበት በኋላም ግማደ መ
ስቀሉን ከነሥርዓቱ የተቀበሉበት
በዚሁ ዕለት ስለሆነ ሁልጊዜ መስከ
ረም አሥር ቀን እንዲከበር አዋጅ
አውጀዋል። ሥርዓትም ሠርተዋል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዓፄ መስ
ቀል በዓል ነገሥታቱ የክብር ል
ብሳቸውን ለብሰው በዙፋናቸው ላ
ይ ይገኛሉ ይገለጻሉ መሳፍንቱና
መኳንንቱ በክብር ተሰልፈው ይ
ታያሉ ካህናቱም የማዕረግ ልብ
ሳቸውን ለብሰው ለዚሁ በዓል የ
ተዘጋጀውን ቀለም በጥዑም ዜማ
ያሸበሽባሉ ።ሊቃውንቱም መካ
ከል እየተመረጡ ልዩ ልዩ ድርሰ
ቶችን ይናገራሉ ። ቅኔም ያበረ
ክታሉ ። በአንዳንዶቹም ሊቃ
ውንት አስተያየት ይህ የዓፄ መ
ስቀል በዓል የገባው ለአበባ በዓል

ለውጥ ነው ይላሉ ።

ይህ የአበባ በዓልም የሚውለው
መስከረም ፳፰ ቀን ነበር በኋላ ግን
ሊቃውንቱ መክረው በአንድ ወር
ሁለት በዓል ማክበር አይቻልም
ብለው መስከረም ፲ ቀን ተደርቦ
እንዲከበር ተደረገ ። ይህ የጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል
ወደ ሀገራችን ከገባና በዓሉም መ
ከበር ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ
እ ነ ሆ እ ስ ከ ዛሬ ድረስ ለሀገ
ራችን በረከትን መስጠቱ ግልጽ
ነው ።

ለነገሥታትም ይህ የመስቀል ኃ
ይል ኃይላቸው ሆኖአል። ነገሥ
ታቱና መሳፍንቱ መኳንቱና ሠራ
ዊቱ ጠላት በተነሣባቸው ጊዜ መ
ስቀልን በፊት በፊታቸው አሰል
ፈው ይዘምታሉ ።

ጠላታቸውንም ድል ይነሣሉ ስለ
ዚህ ይህ የመስቀል በዓል በኢት
ዮጵያውያን ዘንድ በጣም የተወደደ
ሆኖ ይኖራል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ከዚህ ከ
መስቀሉ ፍቅር የተነሣ ሴቶች የ
አንገት መሳሪያቸውንና የእጅ
ቀለበታቸውን በመስቀል ቅርጽ አ
ሠርተው ያስሩታል ። ሰርሜዳቸ
ው ን ም በ ት ም ህ ር ተ መ
ስ ቀ ል ይሠሩታል እጃቸውንና

ግንባራቸውን በመስቀል ቅርጽ እ
የቀረጹ ይታያሉ ።

በወንዶቹም በኩል መቋሚያቸ
ውን የእጅ በትራቸውን በመስ
ቀል ቅ ር ጽ እ የ ቀ ረ ጹ ይ ይ
ዙ ታ ል ። ለሕፃናቱም ብ ሩ ን
መዳቡን እየቀረጹ ያስሩላቸዋል ።
በዚህ ዓይነት የመስቀል በዓል ይ
ከበራል። ይህን የክርስቶስን ግማደ
መስቀሉን የአመጡት ቅዱሳንም
ታሪካቸውና ድካማቸው በኢትዮ
ጵያውያን ዘንድ ሲነገር ይኖራል ።

ዓፄ ዳዊትም በዚህ ግማደ መስ
ቀሉ በዓል ሰማቸው ሲወሳና ሲነ
ገር ይኖራል ። በኢትዮጵያውያን
ዘንድ የታወቁና የተወደዱ የታሪ
ክ ዓምድ የሆኑ ታላቅ ንጉሥ ና
ቸው ።

በዚህ በመስቀል ኃይል በወንዝ
ዳር በመንደር በተራራ በባሕር
የሚኖሩ አጋንንት ተደምስሰዋል
ጠፍተዋል በሀገሪቱም ላይ ጤና ሰ
ላም ከመሆኑ የተነሣ እህሉ ቢዘ
ራ ይበቅላል ምድር ምበረከትንም
ትሰጣለች ልጅ ቢወለድም ያድጋ
ል ። በሽተኛም ከበሽታው የሚፈ
ወስ ሆኗል ። ስለዚህ ይህ የዓፄ
መስቀል በዓል ሁል ጊዜ ሲከበር
ይኖራል ።

መ/ መልአኩ ፈለቀ

www.ethiopianorthodox.org

# የ ደ መ ራ በ ዓ ል

ደመራ ማለት ደመረ ካለው
ከግዕዙ ቃል የወጣ ትርጓሜውም
የተከመረ ወይም የተሰበሰበ ማለት
መሆኑ የታወቀ ነው ።

ይህን የደመራ በዓል የኢትዮ
ጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታከብረው
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በንግ
ሥት ዕሌኒ አድሮ ያደረገውን ገ
ቢረ ተአምራት ለማስታወስና የመ
ስቀልንም ኃይል ለመግለጽ ያህል
ነው ።


ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል
በአይሁድ ምቀኝነት ከመቀበሩ በ
ፊት በቀራንዮ አደባባይ ጥቂት
ቀን ከቆየ በኋላ ክርስቶስ በሞተ
ጊዜ የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ
የተባሉ ደጋግ ሰዎች ጎልጎታ ተብላ
ከምትጠራዋ ልዩ ቦታ ወስደው
ከመቃብሩ አጠገብ አኖሩት በዚ
ህም አይሁድ ሳይቀብሩት ብዙ
ቀኖች ተቀምጦአል ።

ሐዋርያት በኢየሩሳሌም አካባቢ
በሚያስተምሩበት ጊዜ ምንም እ
ንኳን ከአይሁድ ወገን መከራው
ቢጸናባቸውም ስምንቱን ሺህ ማ
ኅበረ እስጢፋኖስን አስከትለው እ
የሄዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በተሰቀለበት ቦታ ከእግረ መስቀል
ሥር በአንድነት እየተሰበሰቡ ይ
ጸልዩ ነበር ።አይሁድ የአለፈው
ጥፋታቸው ወይም ኃጢአታቸው
አልበቃ ብሏቸው ሐዋርያትን ከ
ማሳደድ አላረፉም ። በመጀመሪያ
የዓለምን መድኃኒት ኢየሱስ ክርስ
ቶስን ሰቅለው እንደገደሉት መስ
ቀሉንም ለማጥፋትና ሐዋርያትንም
ከገጸ ምድር ለመበታተን ቁርጥ
ሐሳብ አደረጉ በ ዚ ህ ም ክ
ንያት ሐዋርያት በስም አጠራር የጌ
ታ ወንድም የተባለውን የዮሴፍ
ልጅ ያዕቆብን የኢየሩሳሌም ኤጴስ
ቆጶስ ስለነበር የጌታን መስቀል
በጥንቃቄ እንዲጠብቀው አዘውታ
ል ። እርሱም የሐዋርያትን ትእ
ዛዝ ተቀብሎ ከመስቀሉ ሥር ተ
ደፍቶ እየጸለየ ሌትና ቀን ሲጠብ
ቀውና ሲያስጠብቀው መላ ዘመ
ኑን አሳልፎአል ።

በተጨማሪም እመቤታችን ቅ
ድስት ድንግል ማርያም ጠዋትና
ማታ እየሄደች በመስቀሉ አንፃር
ፊት ለፊት ቁማ በስቂለ ሕሊና ስ
ታለቅስ እየሰሙ ቅዱሳት እንስ
ትም አብረዋት ያዝኑና ይተክዙ ያ
ለቅሱም ነበር ።ይህንንና ይህን
እየተመለከቱ ከአይሁድ ወገን
አንዳንዶች በምቀኝነት ሲነሡ ብ
ዙዎቹ አይሁድ ደግሞ የመሰቀልን
ተአምራት በማየትና የሐዋርያትን
ም ስብከት በመከታተል በክርስቶስ
አምነዋል ።ከዚህ በኋላ የመስቀል
ተአምራት ቀስ በቀስ በመለዋ
ፓልስቲን (ፍልስጥኤም) ተሰማ።

ስለዚህ ቦታውን ለማየትና ከ
መስቀሉ በረከትንለማግኘት ከሩቅ
አገር ብዙ ሰዎች ይመጡ ነበር ።
እንዲሁም በሽተኞች በመስቀል አ
ጠገብ ሲሔዱ ከጽኑዕ ደዌአቸው
ይድኑ ስለነበር ይህየመስቀል ተአ
ምራት በአይሁድ ዘንድ በጣም
አሳሳቢ ሆነ ዕውራን ወደዚህ ቦታ
እየሄዱ በመስቀሉ ሥር ያለውን
አፈር በመቀባት ዓይናቸው በርቶ
ላቸዋል ።ብዙ ልዩ ልዩ ደዌ ያለ
ባቸው ሁሉ በዚሁ ሁኔታ ድነዋል
በመስቀሉም ላይ የሚታየው የ
ድኅነት ብርሃን ሕዝቡን በጣም
ከማስገረሙም በላይ ያላመኑትን
ሰዎች ወደ እምነት ጐዳና መርቷ
ቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



ካህናቱ የደመራውን ጸሎት ሲያደርሱ

በጎልጎታ አካባቢ የነበረው ሕ
ዝብ መስቀሉን ለማየት በብዛት
ይሽቀዳደም ነበር ። እነሆ ከዚያን
ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በ
አንዳንድ ደጋግ ሰዎች እንጅ ብዙ
ተአምራት ሲሠራበት ይታያል። ሐ
ዋርያት በየጊዜው በክርስቶስ መ
ቃብርና መስቀሉ ካለበት እየተ
ሰበሰቡ ሲያስታኰቱ ወይም ሲጸ
ልዩ የተመለከቱ አይሁድ መስቀ
ሉን ለመቅበር ተማከሩ ። ለዚህም
የተንኮል ሥራ ግንባር ቀደም የ
ነበሩት ካህናተ አይሁድ ናቸው ።

በካህናቱ የቀረበው መጥፎ ም
ክር ጉድጓድ አስቆፍረንየክርስቶስን
መስቀል በታች የሁለቱን ወንበ
ዴዎች መስቀል በላይ አመሳቅለን
እንቅበረው የሚል ሐሳብ ነው ።
ይህ ብቻ ሳይሆን የከተማውም ሕ
ዝብ ጥራጊውን እየወሰደ መስቀሉ
በተቀበረበት ላይ እንዲያፈስ በ
ማለት የጠበቀ ሕግ ወጣ ። ሕዝ
ቡም በዚሁ ትእዛዝ መሠረት ማን
ኛውንም ጥራጊ እየወሰዱ መስቀሉ
በተቀበረበት ላይ ለመድፋት ለ
መጣል ተስማምተዋል ።

ከላይ እንደተገለጸው ወዲያውኑ
መስቀል ባለበት በጎልጎታ ትልቅ
ጉድጓድ በአዋጅ ተቆፍሮ የክርስ
ቶስን መስቀል በሥር የፈያታዊ
ዘየማንና የፈያታዊ ዘፀጋም መስ
ቀሎች በላይ ተደርገው ተቀብረ
ዋል ። አይሁድ የሁለቱን ወንበ
ዴዎች መስቀሎች ከክርስቶስ መስ
ቀል ጋር አብሮ እንዲቀበሩ ያደ
ረጉበት ምክንያት ለማሳሳት ሲሉ
መሆኑ የታወቀ ነው ።

ሕዝበ አይሁድ የባለ ሥልጣኖ
ችን ትእዛዝ በማክበር የቤታቸውን
ጥራጊና ማንኛውንም ቆሻሻ እየ
ወሰዱ በመስቀል ላይ በሚደፉበት
ጊዜ ግማሹ ሲደሰት በአንድ በ
ኩል የሚያዝኑና የሚተክዙ ሰዎች
እንደነበሩ የታሪክ መጽሐፍ ይና
ገራል ። በዚህ ሁኔታ እንደ አለ
ከብዙ ዘመን በኋላ የክርስቶስ መ
ስቀል የተቀበረበት ቦታ እንደ ተ
ራራ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር ።

እንደዚህም ሆኖ ብዙ ዘመን ከመ
ኖሩ የተነሣ ከትውልድ ወደ ትው
ልድ እየተላለፈ ዘመኑ ከ፫፻ ዓመት
በላይ በመሆኑ ወደ መረሳት ደርሶ
አል።ስለ መስቀሉ መቀበር አንዳ
ንድ የታሪክ ሰዎች ብቻ ያውቁነበር
እንጂ ማንኛውም ተራው ሕዝብ
ለማወቅ አልቻለም ነበር። ነገር ግን
የእግዚአብሔርን ኃይል የዘመን
ብዛት የአይሁድ ክፋት ሊያስረሳ
ውና ሊአጠፋው ስለአልቻለ በንግ
ሥት እሌኒ አድሮ የመስቀል ኃይል
እንዲገለጽ የእዚአብሔር ፈቃዱ ሆነ
ከዚህ በኋላ መፍቀሬ ሃይማኖት ቅስ
ጠንጢኖስ በ፬ኛው መቶ ዓመት ገ
ደማ በቁስጥንጥንያ እንደ ነገሠ አብ
ያተ ክርስቲያናትን እያጠፉ አብ
ያተ ጣዖታትን በሚያስፋፉ መክ
ስምያኖስና ድዮቅልጥያኖስ በሚ
ባሉ ዓላውያን ነገሥታት የተዘ
ጉትን አብያተ ክርስቲያናት ንግ
ሥት ዕሌኒ አስከፈተች ።

ወዲያውም ወደ ኢየሩሳሌም ሂዳ
አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳነፅና
የተቀበረውንም መስቀል ፈልጋ ለ
ማውጣት ለእግዚአብሔር ብፅዓት
አደረገች ። ለዚህም ለተቀደሰ ተግ
ባር መነሻ የሆነው ልጅዋ ቆስጠ
ንጢኖስ በመስቀል ኃይል በትም
ህርተ መስቀል አምሳል መክስ
ምያኖስን ድል አድርጎ ሮም ገብቶ
የክርስቲያኖችን እምነት በመስበ
ኩና ለክርስቲያኖችም ስለ ሃይማ
ኖታቸው መብት ስለሰጣቸው የ
ወንጌል ቃል በመስበኩ ነው ።

በዚህ መሠረት ንግሥት ዕሌኒ
በ፫፻፲፱ ዓ ም የክርስቶስን መስ



www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊነታቸው የደመራን ችቦ ሲያበሩ

ቀል ትረልግ ዘንድ ብዙ ወርቅና
ብር አስይዛ ሠራዊቷን አስከትላ በ
ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ።
ከዚያም እንደ ደረሰች መስቀሉ
ያለበትን ቦታ ከአይሁድ ወገን
ማንም ሊያሳያት አልፈለገም ።
ስለዚህ ንግሥቲቱ በታውንና አወ
ጣጡንም ለማወቅ ስትል ወደ እ
ግዚአብሔር አመልክታ ብዙ ት
ግል ካደረገች በኋላ የእግዚአብ
ሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል በራ
ዕይ መስቀሉ ያለበትን ቦታ ገልጾ
ላታል ። በተጨማሪም እግዚአ
ብሔር ሊታረክ ያስቀመጠው እ
ንድ በዕድሜ የገፋ ሰው ኪራኮስ
የተባለው አረጋዊ መስቀሉ ያለ
በት ሥፍራ ጎልጎታ መሆኑን
አባቱ ነግሮት ስለነበር እርሱም
በአወቀውና በተረዳው መሠረት
ሁኔታውን አንድ በአንድ ዘርዝሮ ኮ
ረብታውን ለይቶ ይህ ነው ብሎ
አሳይቷታል ። ንግሥቲቱ በራዕይ
የተገለጸላትና የኪራኮስ ቃል አ
ንድ በመሆኑ በዚህ መሠረት ሰ
ዎች ሁሉ ዛሬ እኛ እንደምናደርገው
ያለ የደመራ እንጨት እየያዙ እ
ንዲመጡ አዘዘች ። በዚያም ላይ
ዕጣን ጨምራ በእሳት እንዲቃጠል
አደረገች ።

በዚህ ጊዜ ጢሱ መጀመሪያ ወደ
ሰማይ ከወጣ በኋላ ወደ ታች ተመ
ልሶ መስቀሉ በተቀበረበት ላይ
እንደ ማርያም መቀነት ተተከለ።
ስለዚህ ነው ቅዱስ ያሬድ አይሁድ
የቀበሩት መስቀል ይገኝ ዘንድ ከ
ዕጣኑ የወጣው ጢስ ሰገደ ሲል
የተናገረው ። ንግሥት ዕሌኒ የዕ
ጣኑ ጢስ የአረፈበትን ካየች በ
ኋላ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ
መስቀል ያለው ከዚህ ነው ብላ
መስከረም ፲፯ ቀን ቁፈራውን እ
ስጀመረች ።

ከዚያም ከብዙ ኃዘንና ድካም
በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር መ
ጋቢት ፲ ቀን መስቀሉን ለማግ
ኘት ቻለች ።ለልጇዋ ለቆስጠን
ጢኖስም ደስ ይበልህ የጌታዬን
መስቀል አገኘሁት በማለት የደ
ስታ ደብዳቤ ላከችለት ። እርሱም
ስለመስቀል መገኘት በጣም ደስ
ስለአለው ወዲያውኑ ወደ ኢየሩ
ሳሌም ወርዶ መስቀሉ ከተገኘበት
ቦታ ላይ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን
እንዲሠራ መሠረት ጥሎ ወደ መ
መናገሻ ከተማው ተመለሰ ።

የቤተ ክርስቲያኑም ሥራ እንደ
ተፈጸመ መስከረም ፲፮ ቀን የመ
ስቀል የቅዳሴ ቤቱ በዓል ንግሥት
ዕሌኒና ልጇዋ ቆስጠንጢኖስ በ
ሉበት ተከበረል ። ስለዚህ የኢ
ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ
ክርስቲያን የደመራና የመስቀልን
በዓል በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥር
ዓት ሁሉት ምክንያቶችን በመከ
ተል ታከብራለች ። በሕዝቡም
ዘንድ የበዓሉ ክብር ታላቅ ነው ።
ይኸውም አንደኛ ንግሥት ዕሌኒ
የክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ስ
ትል በ፫፻፳፱ ዓ ም ደመራ አስደ
ምራ ዕጣን አስጨምራ በአደረገ
ችው ክርስቲያናዊ ተግባር መስቀ
ሉን ያገኘችበትን ምክንያት ለማ
ስታወስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክስሮ
ኤል የተባለው የፋርስ ንጉሥ በ
፮፻፲፬ ዓ ም የኢየሩሳሌምን ከተማ
አጥፍቶ፣ አብያተ ክርስቲያናትን አ
ቃጥሎ፣ ሕዝቡን ማርኮ፣ ገንዘቡን
በዝብዞና ዘርፎ፣ በሚመለስበት ጊ
ዜ ዕሌኒ ተቀብሮ ያገኘችውን የክር
ስቶስን መስቀል በወርቅና በዕንቁ
አጊጦ ስለአገኘው ከብዙ ንዋየ
ቅድሳት ጋር ዘርፎ ወስዶት ነበር ።

ነገር ግን ይህ በሆነ በ፲፬ ዓመት
ሕርቃል የተባለው ክርስቲያናዊ ን
ጉሥ ወደ ፋርስ ዘምቶ ክስሮኤስን
ድል አድርጎ መስቀሉን ይዞ ሰ.



www.ethiopianorthodox.org

መለስ በኢየሩሳሌም ያሉ ክርስ ቲያኖች ሁሉ በሕርቃል ኃይል በእግዚአብሔር ረዳትነት መስቀሉ ከምርኮ ስለተመለሰላቸው እጅግ በጣም ተደስተዋል ። ከደስታቸ ውም ብዛት የተነሣ በዕልልታና በሆታ አበባ ይዘው ችቦ አብርተው መስቀሉንና ንጉሡን እንደተቀበሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያ ንም መስከረም ፲፮ ቀንና ፲፯ ቀን ደመራ ደምራ መብራት አብርታ ስለመስቀል የደረሰውን የቅዱስ ያ ሬድን ዝማሬ በመጥቀስ «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰ ማየ እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ መስ ቀል አበራእንደከዋክብትም ሰማይን አስጌጠ እንደ ፀሐይ አሳየ እያለች በይባቤና በዝማሬ የመስቀልን በ ዓል በየዓመቱ ታከብራለች ።

መ/ጎሩይ ለገሠ



www.ethiopianorthodox.org